የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር መመሪያ

# ቁጥር 795/2013

2013 ዓ.ም

# የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር መመሪያ

የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ውጤታማ ምደባ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር የሚያስፈልጋቸው ውስን ሀብቶች በመሆናቸው፤

የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች በቅልጥፍና፣ በፍጥነት፣ በግልጸኝነትና በፍትሃዊነት እንዲሁም የደንበኛውን ደረጃ፣ የባለፈቃዱን ዓይነት እና የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማስረት ያደረገ አድልዎ በሌለበት ሁኔታ መመደባቸውን ሚያረጋግጥ አዳዲስ የቴሌኮሚኒኬሽን ምርቶች እና አገልግሎቶችን ለደንበኞች ተደራሽ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለብሔራዊ የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር ዕቅድ ዝግጅት እና ማሻሻያ አስተዳደራዊ አሰራሮችን ማቋቋም የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮችን እጥረት ለመተንበይ እና በወቅቱ ለማስወገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፤

የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች አጠቃቀም የደንበኞችን ፍላጎት እና መብት እንዳይገድብ ማስታተልና መቆጣጠር ተገቢ ሆኖ በማኘቱ፤

የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ይህንን የቴሌኮሚኒኬሽን የቁጥር መመሪያ በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(11) ፣ 27፣ 28 እና 29 ማስረት አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር መመሪያ ቁጥር 795/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1) **"የምደባ ሁኔታ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ማስረት የተገለጸው የቁጥር ሚደብ ሁኔታ ማለት ነው፡፡
2) **"ምደባ"** ማለት ባለፈቃዱ በተጠቀሱት ሁኔታዎች መሠረት በቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥርን እንዲጠቀም በባለሥልኑ የተሰጠው ፈቃድ ነው፡፡
3) **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 3 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ማለት ነው፡፡
4) **"ሚደብ"** ማለት በቅደም ተከተል የተቀመጡ የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ስብስብ ነው፡፡
5) **"ክፍያ"** ማለት ለቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች የሚከፈል ዋጋ ወይም የታሪፍ ተመን ማለት ነው፡፡
6) **"ኮድ"** ማለት በአንድ ሚደብ ወስጥ ካሉት የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች እጅግ አስፈላጊ አኃዞችን የሚጂጥር የመቁጠሪያ ቁጥር ማለት ነው፡፡
7) **"መጣስ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 49 ወስጥ የተገለጹትን መሟላት የሚገባቸው ማስፈርቶች ማክበር አለመቻል ማለት ነው፡፡

8) "**ተጠቃሚ**" ማለት ኢንተርኮኔክት ያደረገ ወይም አንተርኮኔክት የሚያደርግ ባለፈቃድ ያልሆነ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገር የሚገናኝ ዓለም አቀፍ የግንኙነት ማጣሪያ አቅራቢ ያልሆነ ደንበኛ ማለት ነው፡፡

9) "ኢንተርኮኔክት ያደረገ ወይም አንተርኮኔክት የሚያደርግ ባለፈቃድ" ማለት የራሱን የቴሌኮሚኒኬሽን ሥርዓት ከኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የቴሌኮሚኒኬሽን ሥርዓት ጋር ኢንተርኮኔክት ያደረገ ወይም ኢንተርኮኔክት ለማድረግ የጠየቀ ባለፈቃድ ማለት ነው፡፡

10) "**ባለ ፈቃድ**" ማለት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

11) "**ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ**" ማለት በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅና በየጊዜው የሚሻሻል የኢትዮጵያ የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር ዕቅድ ማለት ነው፡፡

12) "**የኔትወርክ መዳረሻ ቦታ**" ማለት ደንበኛው በደንበኞች የመጠቀሚያ መሳሪያ አማካኝነት ከፈቃድ ሰጪው ኔትወርክ ጋር በአካል የሚገናኝበት ቦታ ማለት ነው፡፡

13) "**ቁጥር**" ማለት ከአንድ የተለየ አገልግሎት እና ተጠቃሚዎች ጋር የተያያዙ ደንበኞችን እና የኔትወርክ መዳረሻ ቦታዎችን ለመለየት የሚጠቅም የአኃዞች ቅደም ተከተል ማለት ነው፡፡

14) "**ቁጥር ማዛወር**" ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ደንበኞች በተመሳሳይ ቦታ ወይም ሥፍራ የሚጠቀሙበትን የስልክ ቁጥር ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ማዛወር የሚችሉበት ሁኔታ ነው፡፡

15) "**አዋጅ**" ማለት የኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ማለት ነው፡፡

16) "**የአጠቃቀም ሁኔታዎች**" ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበት ሁኔታዎች ገደብ ማለት ነው፡፡

17) "**ጥቅም ላይ የዋለ**" ማለት አገልግሎት ላይ የመዋል ሁኔታቸው "በአገልግሎት ላይ" የሚል ማስወቂያ ያላቸው የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥሮች ድርሻ ነው፡፡

18) "**የአጠቃቀም ደረጃ**" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሠረት የተገለጸው የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር የአጠቃቀም ደረጃ ነው፡፡

19) "**የሥራ ቀናት**" ማለት ሥራ የሚከናወንባቸውን የሥራ ቀናት ብቻ ሲሆን ቅዳሜ እሁድ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ በዓል ሆኖ የታወጀን ማንኛውንም ቀን አያካትትም።

## 3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በሚያጋገጥ ቁጥሮችን ማስተዳደር እና ወጤታማ አጠቃቀማቸውን መቆጣጠር ነው፦

1) ቁጥሮች በደንበኞች ወይም በባለፈቃዶች በባለቤትነት የሚያዙ ብሔራዊ ሃብቶች መሆናቸውን፤
2) ቁጥሮች በቅልጥፍና፣ በፍጥነት፣ በግልጸኝነትና በፍትሃዊነት እንዲሁም የደንበኛውን ደረጃ፣ የባለፈቃዱን ዓይነትና የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ አድልዎ በሌለበት ሁኔታ መሰጠታቸውን፤
3) የቁጥሮች እጥረት ሊተነበይ እና በወቅቱ መወገድ መቻሉን፤ እና፣
4) የቁጥሮች አጠቃቀም የደንበኞችን ፍላጎት እንዳይገድብ መከታተልና መቆጣጠር መቻሉን፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ በሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች እና አገልግሎት ሰጭዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) ይህ መመሪያ የአዋጁን አንቀጽ 6፣ ንዑስ አንቀጽ (11) በመከተል የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮችን ለመቆጣጠር፣ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለመመደብ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ይደነግጋል፡፡

3) መመሪያው በብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ መሠረት የቁጥር ምደባን፣ ማስተላለፍን፣ ማዛወርንና አጠቃቀምን በተመለከተ ስርዓት ይቀርጻል ፡፡

4) በዚህ መመሪያ ቁጥሮች ማለት መደበኛውን የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮች እና አጭር ኮዶ ቁጥሮችን ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ብሔራዊ የቁጥር ፕላን

### 5. ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን ማስወቅ

1) ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ ወስጥ የሁሉንም ቁጥሮች ኮዶችና መደቦች የተሻሻሉ የአመዳደብ እና የአጠቃቀም ሁኔታዎችን፣ ለባለ ፈቃዶች የተደረጉ ተጨማሪ ምደባዎች እና ምደባዎቹ መቼ እንደተደረጉ ማያዝ እና ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ወቅታዊ ስራት ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

### 6. የአመዳደብ ሁኔታ

የአንድ መደብ የአመዳደብ ሁኔታ በሚከተሉት መንገዶች ይገለጻል፡ -

1) **"የተመደበ"** – መደቡ ለአንድ ባለፈቃድ የተመደበ እና በባለፈቃዱ ተመላሽ ያልተደረገ ወይም ከባለፈቃዱ ያልተወሰደበት ከሆነ፣
2) **"ሊመደብ የሚችል"** – መደቡ የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ባገናዘበ ሜልኩ በምደባ ወስጥ ለመካተት የሚችል ከሆነ፣
3) **"ለምደባ የሚጠበቅ"** – "ለጊዜው የሚመደብ "የሚል ማለያ ያለውን መደብ ሳይጨምር መደቡ ወደፊት ሊኖር እንደሚችል ሲጠበቅና የአጠቃቀም ሁኔታዎቹን ባገናዘበ ሜልኩ በምደባ ወስጥ ለመካተት የሚችል ከሆነ፣
4) **"ጥቅም ላይ የማይወል"** – ሊከሰቱ የሚችሉ የሰወና የሥርዓት ችግሮችን ለማስወገድ ሲባል መደቡ ከምደባ ወጪ ከሆነ፣ ወይም፡
5) **"ለጊዜው የማይመደብ"** – የቁጥር ሃብቶችን ላልታወቁ የወደፊት ክስተቶች ለማጠቀም ሲባል መደቡ በምደባ ወስጥ ያልተካተተ ከሆነ፣

### 7. አገልግሎቶችን ለማቅረብ ያሉ ወሰንነቶች

1) አገልግሎቱ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት በስራ ላይ ያሉትን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ካላሟላ በስተቀር ባለፈቃዱ አንድን ቁጥር ለአገልግሎት ማስጫት ሊጠቀምበት አይችልም፡፡
2) አንድ ባለ ፈቃድ ለራሱ ያልተመደበለትን ቁጥሮች ወይም ባለሥልጣኑ እንዲጠቀምበት ያለፈቀደለትን ቁጥሮች ማጠቀም አይችልም፡፡

## ክፍል ሶስት

## 8. በብሔራዊው የቁጥር ዕቅድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

1) ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን መከለስ እና ካስፈለገም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚደረግ ማንኛውም ክለሳ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 35-38 ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ አለበት፡፡

## 9. ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ እንዲሻሻል ሚያደርጉ ምክንያቶች

1) ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን ሲከልስ ወይም ሲያሻሽል የሚከተሉትንና ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችን ከግንዛቤ በማስገባት ይሆናል፡-

ሀ) በስራ ላይ ላሉትም ሆነ ወደፊት ለሚጠበቁ አገልግሎቶች በአጭር እና በረጅም ጊዜ የሚኖረውን በፈጣን እድገት ወስጥ ያለ የገበያ ፍላጎት ማሟላት አስፈላጊነት፣

ለ) የቴክኖሎጂ ለወጦችን እና እመርታዎችን፣

ሐ) ከዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት ስምምነቶች፣ ደረጃዎች እና የወሳኔ ሃሳቦች ጋር የመጣጣም ሁኔታ፣

2) ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ ማሻሻያ ሲያቀርብ የሚከተሉትን ምክንያቶች በማካተት እና በእነርሱም ሳይወሰን የሬጉላቶሪ ተጽእኖ ትንተና ማከናወን አለበት፡-

ሀ) የሚደረገው ማሻሻያ በዘርፉና በባለፈቃዱ ላይ የሚያመጣውን ጉልህ ተጽዕኖ፣

ለ) አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቁጥሮች ባለማለወጣቸው ተጠቃሚዎች የሚኖራቸው ጠቀሜታዎች፣

ሐ) ቁጥሮቹን እየተጠቀሙባቸው ባሉት ተጠቃሚዎች ላይ የሚደርስን ያልተገባ ተጽዕኖ፣

መ) ብሔራዊ የቁጥር ዕቅዱን ማለወጥ የሚኖሩትን ጥቅሞችና ወጪዎች፣ እና፣

ሠ) ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን ለማለወጥ ተመሳሳይ ጠቀሜታ የሚሰጡ አማራጮች ወጪዎች፡፡

## 10. ብሔራዊ የቁጥር እቅድ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች የአፈጻጸም ወሰን

1) ባለሥልጣኑ ብሔራዊውን የቁጥር ዕቅድን ለማሻሻል ከሚከተሉት የተወሰኑትን ብቻ ወይም ሁሉንም ሊተገብር ይችላል፡-

ሀ) የአመዳደብ ሁኔታ ማለወጥ፤

ለ) የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ማለወጥ፤ እና፣

ሐ) አኃዞችን በሌሎች በመተካት፣ አዲስ በማስገባት ወይም በማስረዝ ቁጥሮችን መቀየር፡፡

2) ምደባዎችን መፍጠር፣ መደቦችን መሟላስ እና መደቦችን ማሰረዝ የብሔራዊው የቁጥር ዕቅድ ማሻሻያዎች ሳይሆኑ በብሔራዊው የቁጥር ዕቅድ ወስጥ የተያዘና ይፋ የተደረጉ የመደብ አመዳደብ ሁኔታ ለወጦች ናቸው፡፡

## 11. ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ ስለሚሻሻልበት ጊዜ

ባለሥልጣኑ የቁጥር አኃዞችን በሌሎች በመተካት፣ አዲስ በማከገባት ወይም በማሰረዝ ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን የሚያሻሽል ከሆነ፡-

1) ባለሥልጣኑ የማሻሻያ ሥራው ደንበኞች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የሚገልጽ ማስታወቂያ ወይም ምክር አዘል ማስታወሻ በማዘጋጀት ከማሻሻያው ከ6 (ስድስት) ወራት በፊት ለህዝብ ይፋ ሚድረግ አለበት፡፡
2) ባለሥልጣኑ ስለማሻሻያው ለባለፈቃዶች ማሻሻያው ከመደረጉ ቢያንስ ከሁለት (2) ዓመታት በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡ እንዲሁም፣
3) ባለሥልጣኑ ስለማሻሻያው ለዓለም አቀፉ የቴሌኮሚኒኬሽን ህብረትና ለሌሎች ማቸውም አስፈላጊ ለሆኑ የውጭ አገር የቴሌኮሚኒኬሽን አስተዳደሮች ማሻሻያው ከመደረጉ ቢያንስ ከሁለት (2) ዓመት በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡

## 12. ማሻሻዎችን ስለመተግበር

እያንዳንዱ ባለፈቃድ በብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ ላይ የተደረጉትን ማሻሻያዎች በወቅቱና ባለሥልጣኑ በሚወስነው መልኩ መተግበር አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የቁጥሮች አጠቃቀም

## 13. የቁጥሮችን አጠቃቀም ስለመቆጣጠር

1) እያንዳንዱ ባለፈቃድ በየዓመቱ መጨረሻ ላይ ባለሥልጣኑ ለአዲት ሥራ የሚጠይቀውን መረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚፈለገውን መረጃ በሚያቀርብበት ጊዜ ባለፈቃዱ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ በማጠቀም እና ለእያንዳንዱ ምደባ የሚከተሉትን መረጃዎች በማካተት መሆን አለበት፡-

ሀ) እያንዳንዱ የአጠቃቀም ደረጃ የያዘውን ቁጥሮች ብዛት፣

ለ) ምደባውን የሚጠቀሙ አገልግሎቶችን፤ እና፣

ሐ) አጠቃቀምን ለማ ምገም ያመቸው ዘንድ ባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚፈልጋቸውን ሌሎች ማንኛውንም መረጃዎች፡፡

## 14. የቁጥሮችን አጠቃቀም ይፋ ስለሚድረግ

ባለሥልጣኑ በእያንዳንዱ ዓመት ሚዘረሻ ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት ባለፈቃዶች ያቀረቡትን መረጃ ማጠቃለል እና ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

## 15. <u>የአጠቃቀም ደረጃ</u>

ባለፈቃዱ ለተመደቡለት ቁጥሮች የሚከተሉትን የአጠቃቀም ደረጃዎች ማሳየት አለበት፡-

1) **"በአገልግሎት ላይ ያለ"** – ተጠቃሚው በቁጥሩ ላይ ከባለፈቃዱ አገልግሎት እያገኘ ከሆነ፣
2) **"የተሰረዘ"** – ቁጥሩ በዚህ መመሪያ ክፍል ሰባት (7) መሠረት የተሰረዘ ከሆነ፤
3) **"በለይቶ ማቆያ ውስጥ ያለ"** – ቁጥሩ ከዘጠና (90) ቀናት በላይ አገልግሎት ላይ ያልዋለ እና እንዳይሰራ የተደረገ እንዲሁም እንዲሰረዝ የተሰጠውን የዘጠና (90) ቀን በመጠባበቅ ላይ ከሆነ፤
4) **"በአገልግሎት ላይ ያልሆነ"** – ቁጥሩ ለተጠቃሚ ተመድቦ ከዘጠና (90) ቀናት በላይ በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ከሆነ፤ ወይም
5) **"ያልተያዘ"** – ቁጥሩ ለተጠቃሚ መመደብ የሚችል ከሆነ፡፡

**ክፍል አምስት**

**ቁጥሮችን ስለመመደብ**

## 16. <u>ለምደባ የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1) ባለፈቃዱ ቁጥሮች እንዲመደቡለት ለባለሥጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

2) ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ማመልከቻ ሲያቀርብ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀውን ቅጽ መጠቀም እና የሚከተሉትን መረጃዎች መሙላት አለበት፡-

   ሀ) የአመልካቹን ስምና የሚገኝበትን ዝርዝር መረጃ፤

   ለ) ማመልከቻው የሚቀርብበት ፈቃድ፤

   ሐ) ምደባው የተጠየቀባቸው አገልግሎቶች፤

   መ) በምደባው ውስጥ ወደሚከተቱት ቁጥሮች የሚደረግ የስልክ ጥሪና የጽሑፍ መልዕክት የሚከተናገዱባቸው አካባቢዎች፤

   ሠ) በምደባው ወስጥ እንዲካተቱ የተፈለጉ ቁጥሮች ብዛት፤

   ረ) በምደባው ወስጥ እንዲካተቱ የተፈለጉት የቁጥር መደቦች ዓይነት፤

   ሰ) የቁጥር ምደባው ከተሰጠ በኋላ ለሚቀጥሉት ሶስት (3) ዓመታት የሚኖረው የአጠቃቀም ትንበያ፤

   ሸ) ለታሰቡት አገልግሎች ለአመልካቹ የተደረጉ ምደባዎች ካሉ ወቅታዊ የአጠቃቀማቸው ሁኔታ፤

   ቀ) በባለስልጣኑ በምስጢር ሊያዙ የሚገቡ የማመልከቻው ክፍሎች ካሉ መጥቀስ፣

   በ) አመልካቹ ማመልከቻውን ለመደገፍ አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሚላቸውን ማንኛውም ሌሎች መረጃዎች፤ እና፣

ተ) ባለስልጣኑ ማመልከቻውን ለማምገም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው ሌሎች ማንኛውም መረጃዎች፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሽ) የተጠቀሱትን የነባር ምደባዎችን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ለማምገም ሲባል ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) ለባለፈቃዱ ቀደምሙኑ የተመደቡት ቁጥሮች አጠቃቀም ለተመሳሳይ የአጠቃቀም ሁኔታዎች ተገዢ መሆናቸውን፣ እና፣

ለ) የተጠየቁት ቁጥሮች የአጠቃቀም ማጠን ለሞባይልና ከማሽን ጋር ለተያያዙ ቁጥሮች ከሰማንያ በመቶ (80%) ያላነሰ እና ለመልከአምድራዊ እና ሌሎች ከመልከዓምድር ጋር ላልተያያዙ ቁጥሮች ከስልሳ በመቶ (60%) ያላነሰ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## 17. ለምደባ በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ስለሚሰጡ ውሳኔዎች ይዘት

ባለስልጣኑ የምደባውን ማመልከቻ ሊቀበል ወይም ወድቅ ሊያደርግ የሚችል ሲሆን ምደባውን በሚሰጥበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች መሠረት ሊያደርግ ይችላል፤

1) በምደባው ወስጥ የሚካተቱትን ቁጥሮች ብዛት፤ እና፣
2) በምደባው ወስጥ የሚካተቱትን የቁጥር መደቦች፡፡

## 18. የምደባ ማመልከቻዎች የሚገመገሙባቸው መስፈርቶች

ለምደባ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ባለስልጣኑ የሚከተሉትን እውነታዎች ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል፡-

1) ለአመልካቹ ወይም ሌሎች ባለፈቃዶች ምደባን በተመለከተ ከታቀደው አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ ለሆኑ አገልግሎቶች የተሰጡ ማንኛውም የቀደሞ ውሳኔዎች፤

2) አመልካቹ የጠየቀውን አገልግሎት ለማቅረብም ሆነ ቁጥሮች እንዲመደቡለት ብቁ ስለመሆኑ በአመልካቹ ፈቃድ ላይ የተመለከተ ማንኛውም መግለጫ

3) የአጠቃቀም ሁኔታዎች፤

4) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ በስራ ላይ የዋሉ የኮሚኒኬሽን ኔትወርኮች ቁጥር የመተንተን አቅም፤

5) ምደባው ከተሰጠ በኋላ ለሚቀጥሉት ሶስት (3) ዓመታት የሚኖረው የምደባው አጠቃቀም ትንበያ፤

6) በብሔራዊ የቁጥር ዕቅድ ወስጥ በተወሰነው መሠረት ለታቀዱት አገልግሎቶች ለአመልካቹ የተሰጡ ምደባዎች የወቅቱ አጠቃቀም፤

7) የአመዳደብ ሁኔታቸው ላይ **"የተመደበ"** የሚል ማሳያ የሌላቸው የቁጥር መደቦች ብዛትና ክፍፍል፤ እና፣

8) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 49 መሠረት በባለፈቃዱ የተፈጸመ ማንኛውም ጥሰት፡፡

## 19. ለምደባ በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ውሳኔዎች ስለሚሰጡበት የጊዜ ገደብ

1) ባለስልጣኑ የምደባ ማመልከቻዎችን በተቀበለበት ቅደም ተከተል መሠረት መመልከት እና ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

2) ባለስልጣኑ በማመልከቻው ላይ የሚሰጠውን ወሳኔ፣ ማመልከቻው ወድቅ የተደረገበትን ምክንያት ጨምሮ፣ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 20. የምደባ ሁኔታዎች

1) ባለሥልጣኑ ለእያንዳንዱ ምደባ የሚከተሉት መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) ምደባው ከመካሄዱ በፊት በምደባው ወስጥ ያለው እያንዳንዱ መደብ በምደባ ሁኔታው ላይ **"ሊምደብ የሚችል"** የሚል ማሳያ ያለው መሆኑን፤

ለ) በምደባው ወስጥ የተካተቱት እያንዳንዱ መደብ ተመሳሳይ የአጠቃቀም ሁኔታዎች ያላቸው መሆኑን፤

ሐ) ምደባውን እንዲጠቀሙ የታሰበት አገልግሎቶች ተፈጻሚነት ያላቸውን የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ማሟላት መቻላቸውን፤ እና፣

መ) በምደባ ማመልከቻ ወስጥ እየተጠየቀ ያለ የተለየ መደብ ወይም ሌላ መደብ ከሌለ በስቀተቀር በምደባው ወስጥ ያለው እያንዳንዱ መደብ ተመሳሳይ የአጠቃቀም ሁኔታ ካለው ሌላ መደብ ወይም ሌላ ምደባ ጋር መጎዳኘቱን፡፡

2) ምደባዎች ሲደረጉ፣ መደቦች ተመሳሽ ሲደረጉ እና መደቦች ሲሰረዙ በብሄራዊው የቁጥር እቅድ ወስጥ በተናጠል የሚታወቁ መደቦች ሊለያዩ ወይም ሊጣመሩ ይችላሉ፡፡

### ክፍል ስድስት
### ቁጥሮችን ስለመመለስ

## 21. የቁጥር መደቦችን ስለመመለስ

1) አንድ ባለፈቃድ ቁጥሮችን መመደብ ያልቻለበት ምክንያት በማቅረብ እና አዲስ ምደባዎችን የሚያደርግበትን የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ ቁጥሮቹን መመለስ ይችላል፡፡

2) አንድ ባለፈቃድ መደቡን ለመመለስ ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡ ባለፈቃዱ ይህን ሲያደርግ በባለሥልጣኑ የተዘጋጁ ቅጾችን በመሙላት የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፡-፡

ሀ) የአመልካቹን ስም እና የሚገኝበትን አድራሻ ዝርዝር መረጃ፤

ለ) ወደ ባለሥልጣኑ የሚመለሰው መደብ፤ እና፣

ሐ) በመደቡ ወስጥ ላሉት እያንዳንዱ ቁጥር በአጠቃቀም ሁኔታቸው ላይ **"ያልተያዘ"** የሚል ማረጋገጫ፡

## 22. መደቦችን ለመመለስ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ስለሚሰጡ ወሳኔዎች

ባለሥልጣኑ አንድን መደብ ለመመለስ የሚቀርበውን ማመልከቻ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ሊያጸድቅ ይችላል: -

1) ለባለሥልጣኑ የሚመለሱት ቁጥሮች ብዛት፣ እና

2) ወደ ባለሥልጣኑ የሚመለሰው መደብ፡፡

## 23. <u>መደቦችን ለመመለስ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን የሚመመባቸው መስፈርቶች</u>

አንድን መደብ ለመመለስ የሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ወሳኔ ለመስጠት ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን እና ሌሎችንም ጉዳዮች ጭምር ከግንዛቤ ማስገባት አለበት፡ -

1) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ በስራ ላይ የዋሉ የቴሌኮሚኬሽን ኔትወርኮች ቁጥር የመተንተን አቅም፣ እና፣

2) የአመዳደብ ሁኔታቸው ላይ "**የተመደበ**" የሚል ማለያ የሌላቸው መደቦች ብዛትና ክፍፍል፡፡

## 24. <u>መደቦችን ለመመለስ በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ወሳኔዎች የሚሰጡበት የጊዜ ገደብ</u>

1) ባለሥልጣኑ የመደቦች መመለስ ማመልከቻዎችን በተቀበለበት ቅደም ተከተል መሠረት መመልከት እና ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ የሚሰጠውን ወሳኔ፤ ማመልከቻው ወድቅ የተደረገበትንም ምክንያት ጭምር ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

**ክፍል ሰባት**
**ቁጥሮችን ስለማሰረዝ**

## 25. <u>ቁጥሮች የሚሰረዙባቸው ሁኔታዎች</u>

ባለሥልጣኑ አንድን መደብ ከምደባ ሊሰርዝ የሚችለው፡ -

1) በመደቡ ወስጥ ያለው ቁጥር ተፈጻሚነት ያላቸውን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ለሚያሟሉ አገልግሎት ሲውል፣
2) ባለፈቃዱ ቁጥሮቹን ከተመደበለት ሚሊኩ ውጭ ከተጠቀመ፤
3) መደቡ በግልጽ የተለየን ብሔራዊ ጥቅም ለሚጋጋጥ ከተፈለገ፤ ወይም፣
4) ብሔራዊው የቁጥር ፕላን ሲሻሻል ብቻ ነው፡፡

## 26. <u>ቁጥሮችን ለማሰረዝ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ</u>

ባለሥልጣኑ አንድን መደብ ከምደባ የማሰረዙን ሂደትና ምክንያቶች ለባለፈቃዱ ሰረዛውን ከማካሄዱ ቢያንስ ከአንድ (1) ዓመት በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡

## 27. የቁጥሮች ስረዛ አፈጻጸም

ባለሥልጣኑ አንድን መደብ ከባለፈቃዱ ምደባ ለማሰረዝ ማስቡን ለባለፈቃዱ በሚያሳውቅበት ጊዜ፡ -

1) ባለሥልጣኑ መደቡን የማሰረዝ ውሳኔውን ማንሳቱን ካላሳወቀው በስተቀር ባለፈቃዱ በመደቡ ውስጥ ያሉትን ማናቸውንም ቁጥሮች አገልግሎት ላይ ማዋል አይችልም፡፡
2) ባለፈቃዱ በመደቡ ማሰረዝ ምክንያት ተጽዕኖ ለደረሰበት ደንበኛ የስረዛውን ምክንያቶችና በምትኩ ስለሚሰጡት ቁጥሮች ባለሥልጣኑ መደቡን ከማሰረዙ ቢያንስ ከሁለት (2) ወራት በፊት ማሳወቅ አለበት፤ እና፣
3) ባለፈቃዱ በተሰረዘው መደብ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች በሙሉ ባለሥልጣኑ መደቡን ከማሰረዙ ቢያንስ ከአንድ (1) ወር በፊት ከአገልግሎት ማስወጣት አለበት፡፡

### ክፍል ስምንት
### ቁጥሮችን አገልግሎት ላይ ስለማዋል

## 28. ተጠሪን ስለማሳወቅ

እያንዳንዱ ባለፈቃድ ስለ ቁጥር እና ተያያዥ የማዞሪያ እና የትራፊክ ማስፈርቶች ማስታወቂያዎችን ለመቀበል የተመደበውን ተጠሪ ግለሰብ ስምና የመገኛ ዝርዝር መረጃውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 29. የተጠሪን መገኛ አድራሻ መረጃን ስለማስተላለፍ

ባለሥልጣኑ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 ስር በባለፈቃዶች የቀረቡትን ኃላፊዎች ዝርዝር የመገኛ አድራሻ መረጃውን ለጠየቀ ወገን ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 30. ቁጥሮች አገልግሎት ላይ ስለሚውሉበት የጊዜ ገደብ

1) እያንዳንዱ ባለፈቃድ አንድን ቁጥር አገልግሎት ላይ ከማዋሉ ቢያንስ ከአንድ (1) ወር በፊት ከቁጥሩ ወይም ወደ ቁጥሩ የትራፊክ ፍሰት እንደሚኖር ለሌሎች ባለፈቃዶች እና ለማንኛውም የውጭ ሀገር የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ቁጥሮች አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ለማንኛውም ወገን የማሳወቅ ኃላፊነት የለበትም፡፡

## 31. ቁጥሮችን አገልግሎት ላይ የማዋል ሁኔታዎች

አንድ ባለፈቃድ አንድን ቁጥር አገልግሎት ላይ ማዋል የሚችለው፡ -

1) ቁጥሩ ለባለፈቃዱ የተመደበ ሲሆን፤
2) ቁጥሩ ተፈጻሚነት ያላቸውን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ለሚያሟላ አገልግሎት የሚውል ሲሆን፤ እና
3) ቁጥሩ **"ያልተያዘ"** የሚል የአጠቃቀም ሁኔታ ሲኖረው፤

ነው፡፡

## 32. ቁጥሮችን የማዛጋት ሁኔታዎች

ባለሥልጣኑ ከአንድ ቁጥር ወይም ወደ አንድ ቁጥር የትራፊክ ፍሰት እንደሚኖር ለባለፈቃዶች የሚያሳውቀው፡ -

1) ቁጥሩ "**የተመደበ**" የሚል የአጠቃቀም ሁኔታ በሌለው መደብ ወስጥ ከተገኘ፣ ወይም፣

2) ቁጥሩ ተፈጻሚነት ያላቸውን የአጠቃቀም ሁኔታዎች ለሚያሟላ አገልግሎት የዋለ፤

ከሆነ ነው፡፡

## 33. ወደ ቁጥሮች ወይም ከቁጥሮች የሚደረግ የትራፊክ ፍሰት ላይ የተቀመጡ ገደቦች

በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ ባለፈቃድ ሌላ ባለፈቃድ አገልግሎት እየሰጠበት ካለው ወይም ወዳለው ቁጥር የትራፊክ ፍሰትን ማስተላለፍ አለበት፡ -፤

1) ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 መሠረት በተቃራኒው ለባለፈቃዱ ካሳወቀ፣ ወይም፣

2) ቁጥሩ በግልጽ ተቃርኖ ያለው የአጠቃቀም ሁኔታዎችን የሚያሳይ መደብ ወስጥ ከተገኘ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ቁጥሮችን ስለማዛወር

## 34. ቁጥርን ማዛወር ስራ ላይ የሚውልበት ማስፈርቶች

ብሔራዊውን የቁጥር ዕቅድ በማዘጋጀት ወይም የአዋጁን አንቀጽ 28(4) ተከትሎ በሂደት ላይ ባለው ብሔራዊ የቴሌኮሚኒኬሽን ቁጥር እቅድ አስተዳደር እንቅስቃሴ ወስጥ ባለሥልጣኑ ቁጥሮች ማዛወርን በተመለከተ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወሳኔዎችን ወይም አቅጣጫዎችን ሊሰጥ ወይም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ እንደነዚህ ዓይነት ወሳኔዎችን ወይም አቅጣጫዎችን ሲሰጥ ወይም መመሪያዎችን ሲያወጣ የሚከተሉትንና ሌሎችንም ጨምሮ ስለሚኖሩ የአፈጻጸም ሁኔታዎች ከባለፈቃዶች ጋር መመካከር አለበት፤

1) በቁጥሮች እና ለደምበኞች ጥሪና ለሚልዕክት የሚከፈሉ ክፍያዎች መካከል ስላሉት ግንኙነቶች እና ቁጥርን ማዛወር የክፍያ ለወጥ እንዴት እንደሚያስከትል ደንበኛው እንዲረዳ ማገዝ፤

2) የቁጥር ማዛወር ሥርዓት ሥራ ላይ ከዋለ አጠቃቀሙን ማመቻቸት፤ እና፣

3) ቁጥርን ማዛወር መቻል ስለሚኖረው ጠቀሜታ እና የሚያስከትለው ወጪ

## 35. የሚዛወሩ ቁጥሮችን ለመላክ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ለአንድ ቁጥር አገልግሎት የሚሰጥ እያንዳንዱ ባለፈቃድ ቁጥሩ በሌላ ባለፈቃድ አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ማመቻቸት የሚችለው፤

1) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 32 ተከትሎ ባለሥልጣኑ ለአገልግሎት ሰጪው ተቃራኒውን ካላሳወቀ፣

2) ሌላው ባለፈቃድ ለቁጥሩ አገልግሎት ለመስጠት ከተዘጋጀ፣ እና

3) ቁጥሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 መሠረት ቁጥርን ማዛወር ስራ ላይ በዋለበት መደብ ወስጥ ካለ፤

ብቻ ነው፡፡

## 36. የሚዟወሩ ቁጥሮችን ለመቀበል መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

አንድ ባለፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ባለፈቃድ ለተመደበ ቁጥር አገልግሎት ማስጠት አይችልም፡ –

1) አገልግሎቱን ለማስጠት የተዘጋጀው ባለፈቃድ በተሰጠው ፈቃድ ይህንን አገልግሎት ማስጠት የሚችል ከሆነ፤

2) አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ ተጠቃሚው አገልግሎቱን በተባለው ቁጥር ላይ እያገኘ ከሆነ፤

3) ተጠቃሚው አገልግሎቱን ለማስጠት በተዘጋጀው ባለፈቃድ አገልግሎቱን በቁጥሩ እንዲወስድ የተጠየቀ ከሆነ፤ እና፣

4) ቁጥሩ ተፈጻሚነት ያላቸው የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ለሚያሟላ አገልግሎት የሚውል ከሆነ፡፡

## 37. የተዛወሩ ቁጥሮችን ለመመለስ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም ከሌላ ባለፈቃድ በተቀበለው ቁጥር አገልግሎት የሚሰጥ ባለፈቃድ ቁጥሩ ከአገልግሎት ላይ ከተሰረዘ ቁጥሩን ለመጀመሪያው ባለፈቃድ መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል አስር
## ቁጥሮችን ስለማስተላለፍ እና የባለፈቃዶች ቁጥሮችን የመጠቀም መብት ሁኔታዎች

## 38. ምደባዎችን ለማስተላለፍ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1) ባለፈቃዱ ለባለሥልጣኑ በማሳወቅ እና በማጽደቅ ምደባ ለማግኘት ያማከተበትን ፈቃድ ካስተላለፈ፣ የቁጥር ምደባውን ወደ ሌላ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2) የቁጥር ምደባው በሚተላለፍበት ጊዜ፡ –

ሀ) የምደባ መብቶች እና ግዴታዎች ምደባው ወደ ተላለፈለት አካል በቀጥታ ይዛወራሉ፤

ለ) ባለፈቃዱ በተመደቡት ቁጥሮች ላይ ያለውን መብት ያጣል፡፡

## 39. በቁጥሮች መብቶች ላይ ያሉ ገደቦች

ባለፈቃዱ አንድ የንግድ ስምን ወይም የንግድ ምልክትን የሚወክሉ ኮዶች ወይም ቁጥሮች ውስጥ ያሉ መብቶች ጨምሮ በተለዩ ኮዶች ወይም ቁጥሮች ላይ ልዩ፣ ዘላለማዊ ወይም ሌሎች የባለቤትነት መብቶች ማጠየቅ አይችልም፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## ከቁጥሮች ጋር በተያያዘ ያሉ የተጠቃሚዎች መብቶች

## 40. የቁጥር ተጠቃሚዎች የሚቀየሩባቸው ሁኔታዎች

አንድ ባለፈቃድ በአንድ ቁጥር ላይ አገልግሎት የሚያገኝን ተጠቃሚ ወይም አንድ ተጠቃሚ የሚገለገልበትን ቁጥር መቀየር የሚችለው፡ –

1) ቁጥሩ ከመለወጡ በፊት እየተገለገለበት ያለው ተጠቃሚ ቁጥሩ እንዲለወጥለት ጥያቄ ካቀረበ፤
2) ከለወጡ በኋላ ጥቅም ላይ በዋለው ቁጥር አገልግሎቱን ለማግኘት ያሰበ አንድ ተጠቃሚ ቁጥሩ እንዲለወጥለት ጥያቄ ካቀረበ፤
3) ከለወጡ በኋላ ጥቅም ላይ የዋለው ቁጥር ከለወጡ በፊት ከነበረው ቁጥር ጋር አንድ ዓይነት የኔትወርክ መዳረሻ ቦታ የሚያመላክት ከሆነ፤ እና፣
4) ከለወጡ በኋላ ጥቅም ላይ የዋለው ቁጥር ተፈጻሚነት ያላቸውን የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ለሚያሟላ አገልግሎት ጥቅም ላይ ከዋለ፤

ነው፡፡

## 41. የኔትወርክ መዳረሻ ቦታዎች ማለወጥ ላይ ያሉ ገደቦች

በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር አንድ ባለፈቃድ አንድ ተጠቃሚ አገልግሎት የሚያገኝበትን ቁጥር የሚያመላክቱ የኔትወርክ መዳረሻ ቦታዎችን ማለወጥ አይችልም፤

1) በቁጥሩ ላይ አገልግሎቱን እያገኘ ያለው ተጠቃሚ የለውጥ ጥያቄ ካቀረበ፤
2) ቁጥሩ ተፈጻሚነት ያላቸው የአጠቃቀም ሁኔታዎችን ለሚያሟላ አገልግሎት ስራ ላይ እንዲውል ከተፈለገ፤ እና፣
3) አገልግሎት ሰጪው ለደንበኞች አሳውቆ ስምምነታቸውን ካገኘ ነው፡፡

## 42. ለተጠቃሚዎች ስለሚደረግ ማካካሻ

እያንዳንዱ ባለፈቃድ አገልግሎቶቹን በቁጥር አማካኝነት ለሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች በአገልግሎቶቹ ዝርዝር ውሎችና ሁኔታዎች ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡ –

1) ተጠቃሚዎቹ የቁጥሮቹ ባለቤቶች እንዳልሆኑ፤

2) ባለፈቃዱ ለአንድ ተጠቃሚ አገልግሎቱን በሚያገኝበት ቁጥር ላይ፣ ከቁጥሩ ወይም ወደ ቁጥሩ የሚደረግ ጥሪም ሆነ መልእክት ባይኖርም እንኳን፣ አገልግሎቱን እየሰጠ የሚቀጥልበትን ትንሹን የጊዜ ገደብ፤

3) ባለፈቃዱ በቁጥሩ ላይ አገልግሎቱን ማስጠት ቢያቆም ባለ ፈቃዱ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቁጥሮች ላይ አገልግሎት ስለማቋረጡ አግባብ ያለው ማስወቂያ ካልሰጠ በስተቀር አንድ ተጠቃሚ ሊጠይቀው የሚችለውን ማካካሻ፣ እና፣

4) ባለ ፈቃዱ አገልግሎት በሚሰጥባቸውን ቁጥሮች ባለሥልጣኑ በብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች ምክንያት የሚጥላቸውን እገዳዎች ጨምሮ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የሚያቀርበውን አገልግሎት ማቋረጥ አይችልም፡፡

## 43. ስለቁጥር ተጠቃሚዎች ሚሺያ ለማስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች

እያንዳንዱ ባለፈቃድ አንድ ተጠቃሚ አገልግሎት የሚያገኝበት ቁጥር ላይ ለህዝብ ተደራሽ የሆነ ሚሺያ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት ማስጠት አለበት፡ -

1) ባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ የተወከለ ግለሰብ ሚሺያው ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ በጠየቀ ጊዜ፤

2) ባለፈቃዱ በሚሰጠው አገልግሎት ዝርዝር ወሎችና ሁኔታዎች ላይ ሚሺያው ሊሰጥ እንደሚቻል ከገለጸ፤ እና፣

3) ተጠቃሚው ሚሺያው በይፋ እንዲገኝ በግልጽ ፈቃድ ከሰጠ፡፡

## 44. የደዋይ ማስጫ ማሳያ ማሳየት ላይ የተጣሉ ገደቦች

1) አንድ ባለፈቃድ ደዋዩ እንዳይገለጽ ካልጠየቀ በስተቀር ቴክኖሎጂው በሚፈቅደው ወሰን ወስጥ የሁሉንም የአገልግሎቱ ደንበኞች የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር እንዲታይ ማስገደድ አለበት፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም በሚታይ የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር ተንኮል–አዘል ፣ አስጊ ፣ አፀያፊ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆነ ጥሪ የተቀበለ ሰው ባለፈቃዱ የደዋዩን ማንነት እንዲያሳውቀው ማጠየቅ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውም የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር እንዳይታይ የሚቀርብ ጥያቄ በባለሥልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች መጽደቅ አለበት፡ -

ሀ) ጠያቂው ወገን የብሔራዊ ደህንነት ተግባራትን የሚያከናወን ከሆነ፤

ለ) የጠያቂው ወገን ማንነት ግልጽ ሲደረግ ከፍተኛ ተጋላጭነት የሚኖረው ከሆነ፤

ሐ) በባለሥልጣኑ ተገቢ ሆኖ የተገኘ ሌላ ማንኛውም ምክንያት፡፡

4) ባለ ፈቃዱ የተጠቃሚውን የደዋይ ማሳያ ቁጥር ሚደበቅ ጥያቄን ወደጎን በመተው ቴክኖሎጂው በሚፈቅደወ ወሰን ወስጥ የአስቸኳይ አገልግሎት ቁጥሮችን የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር ማሳየት አለበት

5) ባለሥልጣኑ የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር እንዳይታይ ለሚቀርብ ማመልከቻ በሰባት (7) ቀናት ወስጥ ምላሽ ማስጠት አለበት፡፡

5) ማንኛውም የደዋይ ማስጫ ማሳያ ቁጥር እንዳይታይ የቀረበ ጥያቄ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ የሚያገለግለው ለአስራ ሁለት (12) ወራት ሲሆን የእድሳት ማመልከቻ ሲቀርብ ባለሥልጣኑ ሊታደስ ይችላል፡፡

## 45. የተደወለ ማስጫ ማሳያ ቁጥሮችን ማሳየት ላይ የተጣሉ ገደቦች

አንድ ባለፈቃድ የአንድን የተደወለ ማስጫ ቁጥር ማሳያ የተደወለለት ተጠቃሚ እንዳይገለጽ ከጠየቀ እንዲታይ ማድረግ የለበትም፡፡

## ክፍል አስራ ሁለት
## የቁጥር ሃብት የምደባ ክፍያዎች

### 46. የምደባ ክፍያዎችን ስለማሳወቅ

1) በአዋጁ አንቀጽ 29 መሰረት፣ ባለሥልጣኑ በየጊዜው ለቁጥር ሃብት ምደባ የሚጸሙ ክፍያዎችን መወሰን እና ይፋ ማድረግ አለበት፤ እንዲሁም ለቁጥር ሃብት ምደባ የሚጸሙ ክፍያዎችን ሚኒስ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ አለበት፤፡

2) ባለሥልጣኑ የቁጥር ሃብት ተጠቃሚዎች ልዩ የንግድ ጠቀሜታ ያላቸው ኮዶች ወይም የቁጥር መደቦች እንዲመደብላቸው ሲጠይቁ መክፈል የሚጠበቅባቸውን አግባብነት ያላቸው የክፍያ ደረጃዎችን ማውጣት አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚወሰኑት ክፍያዎች እንደዚህ ያሉትን ሃብቶች ወስንነትና ለሁሉም ተደራሽ መሆን መቻል ከግንዛቤ ያስገባ እንዲሁም እነዚህ ሃብቶች ከሚኖራቸው የገበያ ዋጋ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወስጥ ተወዳዳሪና ፈጠራን የሚያበረታቱ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ልማትን ለማበረታታት ክፍዎቹ ከሚገባው ማጠን በላይ መብለጥ የለባቸውም፡፡

### 47. የምደባ ክፍያዎችን ለመወሰን የሚሆኑ መስፈርቶች

1) ለምደባ የሚጸሙ ክፍዎችን ለመወሰን ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በሙሉ ወይም በከፊል ከግንዛቤ ማስገባት አለበት፤

   ሀ) ብሔራዊ የቁጥር ዕቅድን ለማስተዳደር ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን አስተዳደራዊና የስራ ማስኬጃ ወጪዎች፤

   ለ) የአጠቃቀም ሁኔታዎች፤

   ሐ) ምደባዎች በሚሰጡበት ወቅት በሚደረግ የመጀመሪያ ክፍያና ለምደባዎቹ የሚከፈል ዓመታዊ የእድሳት ክፍያዎች መካከል የሚኖር ልዩነት፣

   መ) በስራ ላይ ያሉ ምደባዎችን ወጤታማ አጠቃቀም ማበረታታት፤

   ሠ) ከሚፈለገው ማጠን በላይ ያልሆኑ የቁጥር መደቦች ማጠቀምን ማበረታታት፣

   ረ) "የተመደበ" የሚል የምደባ ሁኔታ ያላቸው ሌሎች መደቦች ተጎራባች የሆኑ መደቦች ማጠቀምን ማበረታታት፤ እና፣

   ሰ) በስራ ላይ ካሉ ምደባዎች ላይ መደቦችን መመለስን ማበረታታት፡፡

2) እያንዳንዱ ባለፈቃድ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የቴሌኮሚኒኬሽን ክፍያ መመሪያ መሠረት ለምደባዎች የተቀመጠውን የመጀመሪያ እና የዕድሳት ክፍያዎችን መክፈል አለበት፡፡

## ክፍል አስራ ሶስት
## ለህግ ተገዢነት፣ ጥሰቶችና ህግን ማስከበር

### 48. ለህግ ተገዢነት

ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ወስጥ ላሉት ድንጋጌዎች ተገዢ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡

## 49. ጥሰቶች

በዚህ መመሪያ ወይም በብሔራዊው የቁጥር ዕቅድ ወስጥ ወይም በማቸውም በሌሎች በአዋጁ ስር የተካተቱ ቁጥር ነክ ግዴታዎችን የሚቃረን ማንኛውም ባለፈቃድ ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

## 50. የህግ ማስከበር እርምጃዎች

1) ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ፣ በአዋጁ እና በሌሎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው የህግ ማዕቀፍ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   ሀ) የገንዘብ መቀጮ ወይም ካሳ ማስጠት፤ እና/ወይም፣

   ለ) ለምደባ የቀረበትን ማንቂያዎች ወደቅ ማድረግ፤

   ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እና ቅጣቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሠረት ፈቃድ ለማገድ ወይም ለማሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች እና ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትሉ የህግ መተላለፍ አይነቶች እንዲሁም የቅጣት ማጠን ለመወሰን በሚያወጣው ደንብ መሠረት አለበት፡፡

## 51. የህግ ማስከበር እርምጃዎችን ለመውሰድ ስለሚያበቁ ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 ስር የተደነገጉትን ሕጋዊ እርምጃዎች ተፈጻሚ ለማድረግ ባለሥልጣኑ ማንኛውንም በከፊልም ሆነ በሙሉ በሌላ ባለ ፈቃድ ምክንያት የሚደርሱ ግዴታን ያለመወጣት ችግሮችን ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል፡፡

## 52. መመሪያ ስለማሻሻል

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ አስቀድሞ ለሁሉም ባለፈቃዶች በማስታወቅ እና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የባለድርሻ አካላት የምክር ሂደት በማካሄድ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡፡

## 53. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከ__________________ 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ _____________ቀን 2013 ዓ.ም.**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**
**የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**